# የህዳሴው ግድብ–አዲሱ የሻዕቢያ የማደናገሪያ ስልት?

ቶሎሳ ኡርጌሳ

Utolosa@yahoo.com

በቅርቡ አውራምባ ታይምስ የተሰኘው ድረ-ገፅ የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮን በመጥቀስ የኤርትራው ፕሬዚዳንት ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሲጠናቀቅ ሀገራቸው ከኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል ልትገዛ እንደምትችል መናገራቸውን በድምፅ አሰምቶናል። ይህ ፅሑፍ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስም በድረ-ገፁ ዘገባ ስር 51 የሚሆኑ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በዚህ አባባል ላይ አስተያየታቸውን ሰድረዋል– ነገርየው የአፍ ወለምታ መስሏቸው 'እርሳቸው ይህን አላሉም' ካሉ ኢሚንት የሻዕቢያ ጭፍን ደጋፊዎች እስከ የሰውዬውን የዕቃ-ዕቃ ጨዋታ ፕሮፖጋንዳ የሚያውቁ በርካታ ግለሰቦች ድረስ።

በእኔ እምነት አቶ ኢሳያስ ይህን የተናገሩት በራሳቸው የመገናኛ ብዙሃን በመሆኑ ጉዳዩን አላሉም ብሎ ማለት ቃለ-ምልልሱን አለማዳመጥ ነው። ምክንያቱም ሰውዬው በቃለ-መጠይቃቸው ላይ ይህ አባባል በሚገባ ስለተናገሩት በዚህ ጉዳይ ላይ ጉንጭ አልፋ ክርክር የሚያስፈልግ አይመስለኝም። ያም ሆነ ይህ ግን ለእኔ ዋናው ነገር አቶ ኢሳያስ በአደባባይ የተናገሩት ነገር አይደለም። ቁም ነገሩ 'እርሳቸው ይህን ያሉት ከምራቸው ነው ወይስ በህዝባቸው ወቅታዊ ጥያቄ ምክንያት ያደረባቸውን ጭንቀት ለማስተንፈስ?' የሚለው ጉዳይ ነው። በሌላ አገላለፅ የአስመራው ፕሬዚዳንት ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን እንደ ጭንቀት ማስተንፈሻ እየተጠቀሙበት ነውን? ብለን መጠየቅ ያስፈልጋል እያልኩኝ ነው።

እናም አባባሉን የኤርትራው መሪ በተለያዩ ጊዜያት የህዳሴው ግድብ አንድ ዋነኛ ማጠንጠኛ በሆነው የአባይ ወንዝ ላይ ከሰጡት አስተያየት እንዲሁም በግብፁ የሙርሲ መንግስት ወቅት ካከናወኑት ድርጊቶች ስንመዝነው፤ አቶ ኢሳያስ የተናገሩት አባባል ውሃ የማይቋጥር ብቻ ሳይሆን "ጥቁር ፕሮፖጋንዳ" (balck propoganda) ሆኖ እናገኘዋለን። እንደሚታወቀው "ጥቁር ፕሮፖጋንዳ" አንድን ዕውነታ ሙሉ በሙሉ ለማሳት የሚቀርብ የውሸት ትንተና ነው። ታዲያ ሰውዬው ህዝቡ 'ኢኮኖሚያችን የደቀቀው ከጎረቤት ሀገሮች ጋር በሻዕቢያ ምክንያት ስለተቆራረጥን ነው' በማለት ያነሳው ጥያቄ ስላስጨነቃቸው ይህንኑ ሁኔታ ለማስተንፈስ ይህን ማለታቸው የሚገርም አይደለም።

እርግጥ የኤርትራ መንግስት በተለያዩ ወቅቶች የላይኛው የተፋሰሱ ሀገራት በተፈጥሮአዊ የውሃ ሀብታቸው እንዳይጠቀሙ ከዘመነ ሙባረክ ጀምሮ እስከ ሙርሲ መንግስት ድረስ በተላላኪነት ሲሰራ የነበረ መሆኑ ይታወቃል። በዚህም ኪራይ ሰብሳቢ ከረጅውን ለመሙላት ያላደረገው የሁከት ሴራ የለም። እናም እንዲህ ዓይነቱ መንግስት በተዘዋዋሪ መንገድ ኢትዮጵያን እንደግፋለን ይነት ዲስኩር ከጊዜ መግዣነት የዘለለ ትርጉም የለውም። ለምን ቢሉ አባባሉ በአሁኑ ወቅት ግብፅ በእርስ በርስ የፖለቲካ ትኩሳት ወስጥ በሆነችበትና በዚህም ሳቢያ እንኳንስ የአቶ ኢሳያስን ሁከት አደራጅነት ልትሰማ ቀርቶ ራሷንም እንደ ሀገር ለማስቀጠል በአስቸጋሪ ሁኔታ ባለችበት ጊዜ የተነገረ በመሆኑ ነው። የአስመራው አስተዳደር ማንነቱን እንዲህ በቀላሉ ቀይሮ ኢትዮጵያም ሆነች ሌሎች የተፋሰሱ ሀገራት በተፈጥሮአዊ ሃብታቸው ተጠቅመው እርሱም ከልማት ትሩፋቱ መጠቀም የሚፈልግ አይደለም–ነብር ዥንጉርጉርነቱን እንደማይቀይረው ሁሉ። እስቲ ለዚህ አባባሌ አስረጅዎችን ከቅርቡ እስከ ቀደምት ድረስ ያሉትንና ሻዕቢያውያን በዚህ ዙሪያ ያላቸውን አቋም በቅደም ተከተል በጥቂቱ እንካችሁ ልበል።…

ጊዜው ምናልባት የሙርሲ መንግስት በግብፅ ጄኔራሎች ሊወድቅ የወራት ዕድሜ ሲቀረው ነው። በወቅቱ አቶ ኢሳያስ ከሙርሲ አስተዳደር ጥሪ ቀርቦልኛል በማለት በአማካሪያቸው በአቶ የማነ ገብረአብ እና በውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸው በአቶ ኡስማን ሳላህ አማካኝነት ለሙርሲ መንግስት ደብዳቤ አስይዘው ወደ ካይሮ ይልካሉ። ታዲያ ቡድኑ እም እንደደረሰ "የግብፅን ታሪካዊ የውሃ ባለቤትነት እንደግፋለን" ይላል። እንግዲህ ልብ በሉ!– ጦር ሰባቂው የኤርትራ መንግሰት የተለመደውን የፀረ-ኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት መዝሙር እያቀነቀነ መሆኑን። አቀንቃኝ ብቻ ሳይሆን በተግባርም የታቻለውን ሁሉ ሊያደርግ የሚፈልግ እንደሆነም ጭምር፡፡ የተቻለውን ብቻ ሳይሆን ከሚችለውም በላይም ተግቶ ለመስራትም ወደ ግብፅ ማምራቱንም፡፡

አዎ! ሁከት አስታቹ አቶ ኢሳያስ በተዘዋዋሪ መንገድ "ዓባይ የኢትዮጵያ አይደለም" እያሉ ነው፤ ለፕሬዚዳንት ሙርሲ የላኩት ደብዳቤ ሲተረጎም፡፡… ነገሩ እንዲህ ነው፡፡ ኤርትራና ግብጽ በዚይን ወቅት አብረው ለመስራት የሁለትዮሽ ስምምነት (bilateral relation) ማድረጋቸው አይከፋም። አብሮ በሰላም መስራት ፋይዳው የበዛ በመሆኑ የሁለቱ ሀገራት ውይይትና ስምምነት በጄ በተባለም ነበር። ግና ምን ያደርጋል?!...ውስጡ ፀረ-ኢትዮጵያ ህዝብነት ተሸረበበት እንጂ፡፡ ታዲያ የወቅቱ ፕሬዚዳንት ሙርሲም በበኩላቸው

ኤርትራ በናይል ጉዳይ የግብጽ "አጋር" ሆና በመቆሟ ደስተኛ መሆናቸውን አስታውቀዋል። ከዚህ በተጨማሪም ግብፅ ከአቶ ኢሳያስ ጋር ጊዜ ሳትውስድ ለመምክር ፍላጎት እንዳላት ተናግረዋል፡፡

ታዲያ ከዚህ ሁኔታ የምንገነዘበው ነገር ቢኖር የአቶ ኢሳያስ ሱስ ሃቅን ድጦ ውሸትን ማንገስ መሆኑን ነው። ይህ ደግሞ እርሳቸው ከግብጽ ጋር በትብብር ለመስራት ደፋ ቀና ማለታቸው በየትኛውም ዲፕሎማሲያዊ ስሌት ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ያመላክታል። በተለይም ነባሩንና የናይል ተፋሰስ ሀገሮችን ሙሉ በሙሉ የበይ ተመልካች የሚያደርገው የቅኝ ገዥዎች ህግን ደግፎ መቆም ማለት የላይኛውን የተፋሰስ ሀገራትን መናቅና የህዳሴውን ግድብ ግንባታ መቃወም መሆኑ የአደባባይ ምስጢር መሆኑ ነው—ነባሩ የቅኝ ገዥዎች ህግ ኢ-ፍትሐዊና የሀገራቱን ተጠቃሚነት የማይቀበል ስለሆነ። ታዲያ እንዲህ ዓይነት መንግስት ዛሬ ድንገት ነሽጦት ከኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል እንገዛለን ማለቱ ከቶ ምን ይሉት የውሸት ድራማ ይሆን?...እርግጥም ነገሩ "ያልወለድኩት ልጄ አባባ ቢለኝ አፌን ዳባ ዳባ አለኝ" የማለት ያህል ነው።

ማንም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚያውቀው አቶ ኢሳያስ የልማት፣ የሰላምና የዴሞክራሲ አጀንዳ የላቸውም፡፡ እናም በወቅቱ በደብዳቤያቸው አማካኝነት ወደ ግብፅ የተጓዙት ለልማት ወይም ለሁለትዮሽ ትብብር እንዳልሆነ የሚያከራክር ጉዳይ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ሰውዬው ከሳህል ተራራዎች ጀምሮ መንግስት እስከሆኑበት ድረስ ስለ ልማት፣ ስለ ሰላምና ስለ ዴሞክራሲ መስማት የሚፈልጉ እንዳልሆኑ የኋላውና አሁን ያለው የሁከት ድርሳናቸው በገሃድ ስለሚናገር ነው፡፡ በመሆኑም የሰውዬው ቀመር ያው የተለመደውን ፀረ-ኢትዮጵያ ህዝብ አቋምን ማቀንቀን ነው—"የጠላቴ ጠላት ለኔ ወዳጄ ነው" ዓይነት ጊዜው ያለፈበት አሮጌ ተረት አራማጅነት፡፡ ግና በዚያን ወቅትም ቢሆን ሰውዬው አልቀናቸውም።

እርግጥ የሻዕቢያው መሪ በደብዳቤም ቢሆን ወደ ግብፅ ያማተሩት ኢትዮጵያና ግብፅ በደም የሚፈላለጉ የሁል ጊዜ ጠላቶች ናቸው የሚል 'ጦር አውርድ' ቀመራቸውን አስልተው ነበር—ነገሩ ነበር ባይሰበር እንዲሉት መና ሆኖ ቀረ እንጂ። ታዲያ እዚህ ላይ እኔም ሁለቱ ሀገራት ታሪካዊ ወይም ኩታ ገጠም ጠላቶች ናቸው እያልኩ አይደለም፡፡ ሀገራቱ ኢትዮጵያዊውን ዘመናትን የተሻገረ የባህል፣ የኢንቨስትመንትና የንግድ ትስስር እንዳላቸው ከማንም የተሰወረ ጉዳይ አይደለም። በተለይም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የሁለቱ ሀገራት የሁለትዮሽ ትብብር እየጎለበተ መጥቷል፡፡...

…ይህ ማለት ግን የማያግባቡን ጉዳዮች አልነበሩም ማለት አይደለም፡፡ ነባራዊው ዓለም እንደሚነግረን ሁሉም ሀገራት በሁሉም ጉዳዮች አይግባቡም፣ በሁሉም ጉዳዮችም አይስማሙም፡፡ የሚያቀራርባቸው ብሔራዊ ጥቅሞች የመኖራቸውን ያህል፣ የማይስማሙባቸውም ቢኖሩ አይገርምም፡፡ ይሁንና አቶ ኢሳያስ የሀገራቱን የግንኙነት ታሪካዊ ዳራ ሳያጤኑ እንዲያው በደፈናው በሀገራቱ መካከል ክፊት ቀዳዳ ፈልገው ሲያሹልቁ አንድም የሙርሲ መውደቅ፣ ሁለትም በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለው ታሪካዊ ዝምድና በማጋደሉ ፍላጎታቸው ሳይሳካ እንደ ጉም በንኖ ጠፍቷል። ያም ሆነ ይህ ግን ከዚህ የሻዕቢያው ፊታውራሪ አሮጌውን የናይል ወንዝ አጠቃቀም "ህግ" በመደገፍ ከግብፅ ጎን የመቆም ጉዳይ የምንረዳው ነገር፣ አቶ ኢሳያስ በቀጥታ የህዳሴውን ግድብ ግንባታ መቃወማቸውን ነው። ግድቡን መቃወም ደግሞ ከግድቡ አለመጠቀም ነው። እናም ሰውዬው ስለ ህዳሴው ግድብ ምን እያሉን ነው?…"እንዲህም አድርጎ ፕሮፖጋንዳ የለም" አሉ እማማ ለምለም።…

አሁን ደግሞ እስቲ አቶ ኢሳያስ የህዳሴውን ግድብ ወደ ተቃወሙበት ሌላኛው አባባል ልውሰዳችሁ—ወደ ኋላ በመጓዝ።…ጊዜው ምናልባትም ከዛሬ ሶስት ዓመት በፊት ነው። በዘመነ ሙባረክ ወቅት። በወቅቱ ኢትዮጵያን ጨምሮ የላይኛው የአባይ ተፋሰስ ሀገሮች /ግብጽንና ሱዳንን ሳይጨምር/ በወንዙ አጠቃቀም ላይ የነበሩትን የቅኝ ግዛት ውሎች የሚተካ አዲስ የስምምነት ማዕቀፍ እየተፈራረሙ ዕለት ነበር፡፡…አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ግን በዚያች ምሽት ተኝተው ያደሩ አይመስሉም፡፡…እንዲያውም "አባይን ተሻግሮ አባይ አለ ወይ፣ ሞትና ፀረ-ልማትነት አንድ አይደለም ወይ?" እያሉ ለራሳቸው ሲያንጐራጉሩ ያመሹ ይመስላሉ፡፡…አይነጋም የለምና ጨለማው በብርሃን ተተካ። የራሱን የጊዜ ዑደት ተወጥቶ ተግባርና ኃላፊነቱንም ለብርሃን አስረከበ፡፡…ታዲያ በማግስቱ "ወዲ አፎም"ም ያደረ አፋቸውን ሳይሽሩና ፊታቸውን ሳይታጠቡ በግብፅ የቴሌቪዥን መስኮት ብቅ አሉ፡፡…በወቅቱ የዚህን ፅሑፍ አቅራቢ ጨምሮ በርካታ ስለ ቀጣናው ልማት የሚያስቡ ሰዎች "እኚህ ሰው ምን ሊነግሩን ይሆን?" የሚል ጥያቄን በመደመም ሲያነሱ አስታውሳለሁ፡፡…

…ታዲያ ሰውዬው እግራቸውን አነባብረው ለግብፁ ጋዜጠኛ "የላይኛው ተፋሰስ ሀገሮች በዓባይ ውሃ አጠቃቀም ላይ የፈፀሙት የተሳሳተ ስምምነትና የመተዳደሪያ ደንብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ይህ ውሣኔያቸው በመካከላቸው ያለውን ችግር ከማባባሱም በላይ

ውጥረት ውስጥ ይከታቸዋል” አሉት።… እኛም ‘ጐሽ የሙባረክ ነጭ ለባሽ’ አልን። እርግጥም የአስመራው ትርምስ ናፋቂ ቡድን መሪ በዕለቱ “ምርጡ” የሙባረክ ነጭ ለባሽ ሆነው ሲደሰኩሩ ነበር። አዎ! አቶ ኢሳያስ የሙባረክን መንግሥት ያረጀ፣ ያፈጀ አስተሳሰብ ጉዳይ ፈፃሚ ለመሆን ሌሊት እንቅልፍ በዓይናቸው ሳይዞር አድሮ፣ ጧት የሙባረክ “የቁርጥ ቀን ልጅነታቸውን” አሳዩን፡፡…

… ኢሳያስ አፈወርቂ ግን “ወይ ፍንክች የአባ ቢላዋ ልጅ” ብለው፣ በየጊዜው በአባይ ወንዝ ጉዳይ የቀድሞው የግብጽ መንግሥት አጋር መሆናቸውን ሲነግሩን ዋሉ፡፡ እኛም ማንነታቸውን ጠንቅቀን ስለምናውቅ “ወዲ አፎም- ለምን?” ብለን አልጠየቅናቸውም፡፡ ምክንያቱም ከእርሳቸው ሊገኝ የሚችል ምላሽ ሊኖር ስለማይችልም ነው። እናም እውነታውን ራሳችን እንዲህ ገላልጠን እንመለከተዋለን፡፡…ውድ አንባቢዎቼ እንደምታውቁት፣ በምሥራቅ አፍሪካ መረጋጋትና ሰላም እንዳይኖር “ሱባዔ” በመግባት ጭምር የሚፀልዩት እኚህ የአሸባሪዎች መሪ፣ በተፋሰሱ ሀገራት ውስጥ “ውጥረት ይፈጥራል” ያሉት በአባይ ወንዝ ምክንያት የቀቢፀ-ተስፋ ጦርነት ናፋቂ ህልማቸው ከሁለት ምክንያቶች የመነጨ ነው፡፡ አንደኛው የቀድሞውን የግብፅ መንግሥት በመደገፍ ለፀረ-ሰላም ኃይሎች የጥፋት ተልእኮ የሚውል ገንዘብ ማግኘት ሲሆን፣ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ “ሁሉም ሀገራት ይሳሳታሉ፣ የእኔ አመራር ግን ትክክል ነው” ከሚል አላዋቂ ግብዝነት የመነጨ ነው፡፡

ሰውዬው በአባይ ወንዝ ሳቢያ በተለይም ግብጽና ኢትዮጵያ ውጥረት ውስጥ ቢገቡ ተጠቃሚ እሆናለሁ ብለው የሚያስቡ የነውጥ ተስፈኛ ናቸው፡፡ ማንም የዚህ ጽሑፍ አንባቢ እንደሚገነዘበው፣ የቀድሞው የግብጽ መንግሥት ኢትዮጵያ ሰላም ከሆነችና ከተረጋጋች አባይን ልትገድብ ትችላለች በሚል ተቀባይነት በሌለው ኢ-ፍትሐዊ እሳቤ የኤርትራን መንግሥት በነጭ ለባሽነት ሲያሰማራው ቆይቷል፡፡ አቶ ኢሳያስም በ“ጭር ሲል አልወድም” ባህሪያቸው እንደ ውሃ ቀጂ በየቀኑ ካይሮ እየተመላለሱ፣ ሀገራችንን እንዴት ማተራመስ እንደሚቻል ለሙባረክ ማብራሪያ በመስጠት ባተሌ ሆነው ቆይተዋል–የዛሬን አያድርገውና። ለዚህ ተግባራቸውም በወረታው ዶላሮችን የሚቃርሙት የአሸባሪዎቹ መሪ፣ ሀገራቱ በአባይ ወንዝ ዙሪያ ስምምነት ላይ ከደረሱና ሰላም ከወረደ “የእንጀራ ገመዴ ይበጠሳል” በማለት የሚሰጉና “የዕለት እንጀራዬን ብጥብጥ አድርገው” እያሉ የሚያላዝኑ ግንባር ቀደም ተላላኪ መሆናቸው ፀሐይ የሞቀው ሃቅ ከሆነ ሰነባብቷል፡፡

ምንም እንኳን ሰውዬው በቀድሞው የግብፅ መንግሥት እየታገዙ የኢትዮጵያ ፀረ-ሰላም ኃይሎችንና ሽብርተኞችን በመመልመል፣ በማደራጀት፣ በማሰልጠንና ወደ ሀገራችን አስርገው በማስገባት እድገታችንን ለማሠናከል ቢወጡና ቢወርዱም፣ ተስፋቸው ግን ጉም ከመዝገን የዘለለ አልሆነም፡፡ ከንቱ መፍጨርጨራቸው በመንግሥታችን በሳል አመራር፣ በሕዝባችን ንቁ ተሳትፎ እንዲሁም በጀግናው የመከላከያ ሠራዊታችንና በፀጥታ ኃይሎች ቅንጅታዊ ሥራ እንዳያንሰራራ ተደርጎ ድባቅ ተመትቷል፡፡

ሁኔታውን አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ በአባይ ጉዳይ ላይ በወቅቱ "የጦርነት ተንታኝ" ሆነው የከረሙበት ሌላኛው ምክንያት ደግሞ የሰውዬው ግብዝ አላዋቂነት ነው፡፡ በእርሳቸው አስገራሚ አስተሳሰብ የምስራቅ አፍሪካ መንግስታት ሁሉ የተሳሳተ መንገድን የሚከተሉ ሲሆን፣ ሰውዬው ግን ብቸኛውና ትክክለኛው መሪ ነኝ ብለው የሚያስቡ ናቸው፡፡…ለነገሩ አበው "ድሃ በህልሙ ቅቤ ባይጠጣ ኖሮ፣ ንጣት ይገድለው ነበር" ያሉት ይትብሃል ዝም ብለው የተናገሩት አይደለም–ለእንዲህ አይነቱ የቅዥት ዓለም ሰው ምላሽ እንዲሆን አስበው ይመስለኛል፡፡…ያም ሆነ ይህ ግን የሰውዬው የማንነታዊ ልኬት በግልፅ የሚታወቅ ነው።…

… እንደሚታወቀው እርሳቸው የሀገራቸውን ህዝብ ነፃነትን፣ እኩልነትንና ፍትሕን እንደ እህል ውኃ እንዲጠማ ያደረጉ እንዲሁም ልማትንና ዕድገትን ብሎም ምርጫን ከጎረቤት ሀገሮች እንዲሰማ ብቻ የፈረዱበት አምባገነን መሪ ናቸው፡፡ ሌላው ቀርቶ በአንድ ወቅት የራሳቸው ዜጎች በሚመላለሱበት ካይሮ ውስጥ ሰላማዊ ሰልፍ የወጡባቸው ግለሰብ ናቸው። በዚያን ወቅት "መሰሪ አልየውም" የተባለ የግብፅ ድረ-ገጽ ይፋ እንዳደረገው፣ ኤርትራዊያን አዲስ ህገ-መንግሥት እንዲረቀቅና ነፃ የምክር ቤት ምርጫ እንዲካሄድ በመጠየቅ ካይሮ የሚገኘው የአቶ ኢሳያስ ኤምባሲ ውስጥ የመሸጉ ሹማምንቶቻቸውን አፋጠዋቸዋል፡፡… ይህ ደግሞ እንዴት የጥሩና የተወዳጅ መሪ መገለጫ ሊሆን እንደሚችል የሚያውቁት ሰውዬው ብቻ ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪም ሰውዬው ሕዝባቸውን ላለፉት 22 ዓመታት ለእርዛት፣ ለድህነትና ለድንቁርና የዳረጉት "ምርጥ መሪ" ስለሆኑ ነውን? ብለን ስንጠይቅም፤ የምናገኘው ምላሽ አቶ ኢሳያስ በሌላቸው አቅም በግብዝነት የሚመፃደቁ ከመሆናቸውም በላይ፤ እውነተኛ ብቃታቸው ተፍቆ ሲታይ ሌላ መሆኑ ነው፡፡ እርሱም በግብረ-ሽበራ ሥራ የአል-ሸባብን ስራ ያለ አንዳች አማካሪ ሊሰሩ የሚችሉ "ምርጥ መሪ" መሆናቸው ብቻ ነው፡፡ እንዲያውም

ሰውዬው በአሁኑ ወቅት በመዳከም ላይ ያለውንና የምስራቅ አፍሪካውን የአል-ቃዒዳ ክንፍ አል-ሸባብን ሙሉ ስራ ተክተው የመስራት አቅም አላቸው ማለት ይቻላል። እንዲያውም ያኔ ምናልባትም አሳማ ቢን ላደን ሲሞትና አል-ቃዒዳ አመራሩን ለመምረጥ በሚሯሯጥበት ወቅት እርሳቸው ውስጥ ለውስጥ ለመወዳደር ሳይፈልጉ የቀሩ አይመስለኝም። ይሁንና "አል-ሸባብን" እየመሩ ስለሆኑ፣ በሥልጣን ላይ ሥልጣን ላለመደረብ ብለው ሳይተውት የተውት ይመስለኛል።...ሆ!...ሆ!...ውይ የእኔ ነገር!...ምኑን ያሳስበኛል ጃል?! ለካስ ሰውዬው "ምርጫ" የሚባል ነገር አይወዱምና!....ያም ሆነ ይህ ግን ሰውዬው በዚህኛውም የህዳሴው ግድብ ተቃውሟቸው

...ያም ሆነ ይህ እስቲ ወደ ተነሳሁበት የህዳሴው ግድብ የተምታታ ሃሳባቸው ልውሰዳችሁ፡፡...ቀደም ባሉት ጊዜያት ከነግብፅ ጋር ቤተኛ ሆነው "በአባይ ጉዳይ የግብፅ ደጋፊ ነን" ሲሉ የነበሩት ኢሳያስ አፈወርቂ፤ ከሙባረክ አገዛዝ በኋላ ምን እንደነካቸው ሳይታወቅ ድንገት ብንን ብለው በራሳቸው መገናኛ ብዙሃን "የኢትዮጵያ ሕዝብ በአባይ ውኃ መጠቀም አለበት" አሉ። ጊዜውም ከዛሬ ሁለት ዓመት በፊት ነው።...ታዲያ በወቅቱ ሰውዬው ሕዝባቸው ምንም መረጃ እንዳያገኝ አድርገው ስለ ሰሜን አፍሪካና መካከለኛ ምሥራቅ ቀውስ መናገር ያለብኝ እኔ ብቻ ነኝ" በማለት በገዛ ቴሌቪዥናቸው ይህን ማውራታቸውን ስሰማ "ወቸው ጉድ!" ከማለት ውጭ ሌላ አማራጭ አልነበረንም፡፡ ...እርግጥም የማምታታት አክሮባታቸው ይደንቃል።...

ግና እንደ እኔ ይህን አባባላቸውን የሰማ ሰው በየዋህነት "ሰውየው ስለ ኢትዮጵያ በጎ ነገር ያስባሉን?" የሚል ጥያቄ አንስቶ ከራሱ ጋር ውዝግብ ሊገጥም ይችላል፡፡ እንዲያውም "ሻዕቢያ በሀገራችን ላይ የሚከተለውን ፖሊሲ ቀየረ እንዴ?" በማለት የሚያሰላስል የዋህ ግለሰብም ሊኖር ይችላል፡፡... እርግጥ የሰውዬውን የማደናገሪያ ንግግር በዚህ መልኩ የሚመለከት ሰው ካለ፣ እውነት...እውነት እላችኋላሁ ያ ግለሰብ "ሞኝና ተላላ" ነው፡፡ ምክንያቱም እውነታውና የኢሳያስ ማደናገሪያ ለየቅል በመሆናቸው ነው፡፡ የአስመራው አስተዳደር የሀገራችን ደመኛ ጠላት እንዲሁም ዛሬም ቢሆን ኢትዮጵያን የማተራመስ ፖሊሲውን ያልቀየረ የጥቂቶች ስብስብ ነውና፡፡...

...ይህ ሃቅም አቶ ኢሳያስ የዚያ ዕለት ድንገተኛ ንግግራቸው፤ "...የኢትዮጵያ የውኃ መጠን ብዙ ነው፣ አነስተኛ ነው የሚለው ትርጉም የለውም" በማለት ቀደም ሲል "በውኃው

መጠቀም አለበት” ሲሉ የተናገሩትን በቀጥታ በማፍረስ አረጋግጠውልናል፡፡ ይህም የሰውዬውን እውነተኛ ፍላጐት ፍንትው አድርጐ የሚየያሳይ ነው፡፡ በእኔ እምነት “የአስመራው ነውጤ” ንግግር ከወትሮው ያልተለየ፣ የቅርብና የሩቁን ያላገናዘበና ዕይታ የሌለው ግልብ ዲስኩር ነው፡፡ ታዲያ ይህ አባባል እንዳለፉት ዲስኩሮች ሁሉ ምንም ዓይነት ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ መሠረት የሌለው ከመሆኑም በላይ፤ ሰውዬው የሁኔታዎች ግብታዊ ሰለባ የሆኑና ፍራቻ እንደነገሰባቸው ብቻ የሚያመላክት ነው፡፡

አንድ ጤነኛ አዕምሮ ያለው ሰው በወንዙ የመጠቀም መብትን እየገለፀ ባለበት አንደበቱ፣ ተመልሶ ፍትሐዊ ክፍፍልን የሚወስነውን የውሃ መጠን “ትርጉም የለውም” ሊል አይችልም፡፡ ታዲያ ይህ የአቶ ኢሳያስ የማምታታት ተግባር ሻዕቢያ እውነተኛ ፍላጐቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በጎ ነገር ማሰብ ሳይሆን፣ የተለየ የጥፋት መንገድን እየተከተሉ ለመሆኑ አመላካች ነው፡፡ ስለሆነም የአስመራው መሪ ከዚህ በፊት በይፋ ይገልፁት የነበረውን የጥላቻ መንፈስ፣ በማደናገር አካሄድ ቀይረውት በአዲስ መልክ አጠናክረው መቀጠላቸውን የሚገልፅ ከመሆኑ ውጭ ሌላ የሚያስረዳው ነገር የለም፡፡

ለነገሩ ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ ተጠቅማ የህዳሴውን ግድብ የመገንባት መብቷን ተፈጥሮአዊም ይሁን ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ስለሚፈቅዱላት የማንንም ማረጋገጫ ማግኘት አትሻም፡፡ እንኳንስ ለራሳቸው ተራ የፕሮፖጋንዳ ፍጆታ የሚዘባርቁት ኢሳያስ አፈወርቂ ቀርቶ፣ የትኛውም ወገን ቢሆን “መብቷ ነው” ቢልም፣ ባይልም የሚያመጣው አንዳችም ነገር የለም፡፡ አባባሉም የአስመራው መንግስት “ፖሊሲውን ቀይሯል” የሚያስብለውም አይደለም። የኤርትራ ባለሥልጣናት በመሪያቸው አስተባባሪነት የኢትዮጵያን መንግሥትና ሕዝብ ሰላም የማይፈልጉ ፀረ-ሰላም ኃይሎችን እያስታጠቁና አስርገው የማስገባት ሙከራዎች ላይ ተጠምደው የሚገኙ በመሆናቸው፣ የፖሊሲ ለውጥ አድርገዋል ብሎ  ማሰብ የዋህነት ነው— የትናንትም ይሁን የዛሬ ፖሊሲያቸው ትርምስና ትርምስ ብቻ ስለሆነ፡፡

ታዲያ ከዚህ አጠቃላይ ሁኔታ ተነስተን ‘የህዳሴው ግድብ—አዲሱ የሻዕቢያ የማደናገሪያ ስልት ነውን?’ ብለን ስንጠይቅ፤ በእኔ እምነት ምላሹ “አዎ” የሚል ይሆናል። ምክንያቱም ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደሞከርኩት የኤርትራ መንግስት ግድቡን የመገንባት አስኳል ጉዳይ በሆነው በዓባይ ጉዳይ የሚሰጣቸው የማደናገሪያ ሃሳቦች ከጊዜው

ጋር እየተዛመዱ የሚነገሩ እንጂ እውነተኛው የአቶ ኢሳያስ መንግስት መገለጫ ባለመሆናቸው ነው። አመቺ ሁኔታ ሲያገኙና ግብፅ ውስጥ መረጋጋት ሲፈጠር ትክክለኛ አቋማቸውን የሚያንፀባረቁበት፣ ሁኔታው የተገላቢጦሽ ሲሆን ደግሞ የቀበሮ ባህታዊ ሆነው ብቅ የሚሉበት የማደናገሪያ ስልት ነው። ለዚህም ነው ሰውዬው ከመሰንበቻው በሌለ ማንነታቸው ከኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል እንገዛለን…ምንትስ በማለት የደሰኮሩት።

እናም በእኔ እምነት የኤርትራ መንግሥት ከኢትዮጵያ አንፃር የአቋም ለውጥ አድርጓል ተብሎ የሚወሰደው፣ እያከናወነ ካለው አፍራሽ የትርምስና የትንኮሳ ተግባር እንዲሁም ከአሸባሪዎች ጋሻ ጃግሬነት ራሱን አላቅቆና "አሉ" የሚላቸው ችግሮች ካሉ /የሚኖሩ አይመስሉኝም/ በውይይትና በድርድር ለመፍታት ዝግጁ ሲሆን ብቻ መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡ ከዚህ ውጪ የአስመራው መሪ "ዓይኔን ግንባር ያድርገው" በሚል ቅጥፈት አዲስ የደበሎ ለምድ ለብሰው ብቅ ባሉበት ርካሽ ፕሮፖጋንዳ ሻዕቢያን እንደ ጥላ ሲከተለው የኖረውን የብጥብጥ አባዜ ሊቀይረው እንደማይችል ሊረዱ ይኖርባቸዋል ባይ ነኝ፡፡

ለነገሩ አቶ ኢሳያስ በእውነተኛ ባህሪያቸው ታላቁን የህዳሴ ግድብ ለማደናቀፍ በተላላኪነት ውጤት አልባ ሴራቸውን ቢከውኑ አሊያም በማደናገሪያ ስልታቸው ያሻቸውን እንደ አሚና ቢለፍፉ፤ ሀገራችንንና ህዝቦቿ የጀመሩትን ታላቁን የህዳሴ ግድብ ከመገንባት ለአንድም ሰከንድ ቆም አይሉም። የሚያግዳቸው አንዳችም ዓይነት ምድራዊ ኃይል የለም። ለምን ከተባለ፤ ህዳሴውን በቅርበት ለማየት የሚሻውና ከጫፍ እስከ ጫፍ ለግንባታው በሁሉም ዘርፎች ተነቃንቆ ውጤታማ የሆነው የሀገራችን ህዝብ እንዲሁም መሪው ልማታዊው መንግሰት ከምንጊዜውም በላይ ተቀናጅተው "የነብርን ጭራ አይዙም፣ ከያዙም አይለቁም" ካሉ ከሁለት ዓመት ተኩል በላይ ስለሆናቸው ነው። ይህ የጋራ ልማታዊ ክንድ ደግሞ ሁሉንም ጊዜው ያለፈባቸውን ሻዕቢያዊ ቴክኒኮችን አብጠርጥሮ ስለሚያውቅ በአቶ ኢሳያስ የተለመደ የማደናገሪያ ስልት የሚታለል አይደለም። እናም የሰውዬው ሰሞነኛ አባባል "ሁሉ አማረሽን ገበያ አታውጧት" ከመባል የሚዘል አይደለም። ምክንያቱም "ወዲ አፎም" ከትናንት እስከ ዛሬ እየከወኑት ያሉት የሚታወቅ ድራማቸው 'ሲቀዘቅዝ በእጅ፣ ሲሞቅ በማንኪያ' እንዲሉት ዓይነት በመሆኑ ነውና። ቸር እንሰንብት።